ኢዮቤልዩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡

አዲስ ፡ አበባ ፡

በሀገራችን ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ የተደረገውን ፡ እርምጃ ፡ በተጨማሪ ፡ የሚያስረዳ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ታትሞ ፡ ሲወጣ ፡ በማየታችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ። ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጀምሮ ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ቅርስና ፡ ባህል ፡ የተመሠረቱት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንና ፡ ሌሎችም ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታችን ፡ በየጊዜው ፡ ተሰናድተው ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውሉና ፡ የሕግም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በዘመናዊ ፡ መንገድ ፡ ሲሠራበት ፡ በማየታችን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። ደጋግመን ፡ እንደገለጽነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በምታደርገው ፡ ፈጣን ፡ የዕድገት ፡ እርምጃ ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ አገልግሎት ፡ ስለሚፈልግ ፡ ሕጉ ፡ በደንብ ፡ እንዲሠራበት ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ለማስተማር ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተቋቋመ ። የፍርድ ፡ ቤቶቻችን ፡ የሚሰጡትን ፡ ፍርድና ፡ ስለኢትዮጵያም ፡ ሕግ ፡ የሚገልጡትን ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ አስተያየቶች ፡ የሚገልጽ ፡ መጽሔት ፡ መውጣት ፡ ተጨማሪ ፡ እርምጃን ፡ የሚያስገኝ ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ እንተማመናለን ።

ሕግ ፡ በአንድ ፡ አገር ፡ የአንድነት ፡ ኃይል ፡ ነው ። ዘማናዊ ፡ ሕጎችን ፡ በማውጣት እንዲፈጸሙ ፡ ከታቀዱት ፡ ዓላማዎች ፡ አንዱ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ አንድነት ፡ እንዲመሠረት ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። ሕጉ ፡ በትርጉም ፡ ምክንያት ፡ ሲያጠራጥር ፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ ሕግ ፡ ያልወጣለት ፡ ጉዳይ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕጉን ፡ መተርጐምና ፡ በሥራም ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚውል ፡ መወሰን ፡ ይገበቸዋል ። እነዚህም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዶች ፡ በሕግ ፡ አስተዳደር ፡ በኩልና ፡ ለሕግ ፡ ዕድገት ፡ ለሚሠሩ ፡ በሙሉ ፡ መታወቅ ፡ አለባቸው ። የፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዶች ፡ ታትመው ፡ መውጣት ፡ ሕጉን ፡ በበለጠ ፡ እርግጠኛና ፡ ግልጽ ፡ ያደርጉታል ። ይህም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ዕድገት ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ።

